- **<u>ሚስጥራዊነት፦</u>** መረጃን መግለጽ በህግ የተገደደ ወይም ኮሚሽኑ በቀረበለት ቅሬታ ላይ የምርመራ ስራ እንዲሰራ መረጃ መሰጠት ከሌለበት በስተቀር፣ የኮሚሽኑ እና የ Technion ሰራተኞች ጉዳዩን በሚመለከት መረጃን መግለጽ አይችሉም።
- **<u>ቅሬታ ማቅረብ የሚችለው ማነው፣ ቅሬታ እንዴት ይቀርባል፣ ለማን እናሳውቅ፦</u>** ጾታዊ ትንኮሳ ወይም ከጾታዊ ትንኮሳ ጋር የተያያዘ ጥቃት የተፈጸመበት ወይም ሌላ የ "Technion ሰራተኛ" በዚህ ተግባር ላይ ተሳታፊ ነው የሚል ጥርጣሬ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታ እንዲያቀርብ ይጋበዛል፣ ይጠየቃልም። "የTechnion ሰራተኞች" የሚባሉት፦

  በ Technion ፕሮግራሞች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች (የአካዳሚክ መሰናዶ ፕሮግራሞች እና በእረፍት ጊዜ ላይ ያሉ ተማሪዎችን ጨምሮ)፣ አካዳሚክ መምህራንና ሰራተኞች (ነባር፣ ጁኒየርና ተጋባዥ መምህራን)፣ የምርምር ቡድን አባላት፣ የአስተዳደር ሰራተኞች (ቋሚ እና ጊዜያዊ ሰራተኞች፣ የኮንትራት አማካሪዎች፣ አገልግሎት አቅራቢዎች እና ሰራተኞቻቸው)፣ የ Technion በጎ ፈቃደኞች እና ጡረተኛ የ Technion ሰራተኞች ናቸው።

  **ቅሬታዎች ለኮሚሽነር (በቅሬታ አቅራቢው የተመረጠ) መቅረብ ያለባቸው በጽሁፍ (ኢሜይል) ወይም በስልክ ወይም በአካል** ወይም ለዘርፉ አስተባባሪ (ስምና የኢሜይል አድራሻ ከታች ይመልከቱ) መላክ አለበት። ኮሚሽኑ እና የተለያዩ የዘርፍ አስተባባሪዎች በፍላጎታቸውና በሕጉ መሰረት ክስተቶችን ሪፖርት የሚያደርጉና ቅሬታ የሚያቀርቡ ሰዎችን ሚስጥራዊነት ያከብራሉ።

**ኮሚሽኑ**

**አስተባባሪ ኮሚሽነር** (ትንኮሳን የመከላከልና የመከባበር ባህልን የማጎልበት ሃላፊነት ያለበት። ምክር ይለግሳል፣ ቅሬታዎችን ያስተናግዳል)

**Professor Tal Alon-mozes** **ስልክ:** 052-2492970 artal@technion.ac.il

**ኮሚሽነር** (ምክር ይለግሳል፣ ቅሬታዎችን ያስተናግዳል)

**Liat Reter ስልክ፦** 04-8295680 liatre@technion.ac.il

**የሕክምና ፋኩልቲ ኮሚሽነር** (ትንኮሳን የመከላከልና የመከባበር ባህልን የማጎልበት ሃላፊነት ያለበት። ምክር ይለግሳል፣ ቅሬታዎችን ያስተናግዳል)

**Dr. Anat Ilivitzki ስልክ፦** 052-6330032 a.ilivitzki@rambam.health.gov.il

**ኮንሰልታንት ኮሚሽነር Prof. Naomi Carmon** 052-2614045 carmon@technion.ac.il

**ሰነዱን ያነበብኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።**

..........................................................................................

**ፊርማ**

# ጾታዊ ትንኮሳን በተመለከተ ከ Technion የስነ ምግባር ደንብ የተወሰደ ጽሁፍ
# ምክር እና ቅሬታ የተመለከቱ ጉዳዩች የሚስተናገዱበት

ቀጣዩ ሰነድ ከዋናው ሰነድ የተወሰደ ቁንጽል ሃሳብ ብቻ ነው

በ Technion ውስጥ ጾታዊ ትንኮሳን ለመከላከል በእብራስይጥ ቋንቋ የተጻፈው ጽሁፍ የጸና ይሆናል

የስነ ምግባር ደንቡ በሁሉም ጾታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፣ የወንድና የሴት ጾታዎችም በተለዋዋጭነት ጥቅም ላይ ይውላሉ

- ከ Technion ግቦች መካከል አንዱ ለማጥናት፣ ለማስተማር ወይም ለመሥራት **ወደ መግቢያ በሩ የሚገባ ሁሉም ሰው በአክብሮት የሚስተናገድበት አካባቢ መፍጠር ነው፡- ከጾታዊ ትንኮሳ እና ከዚሁ ጋር ከተያያዘ ጥቃት የጸዳ አካባቢ።** አንድ ሰው ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ከተፈጸመበት፣ ተጎጂው ክብሩን፣ ነጻነቱን፣ ግላዊ መብቱንና የጾታ እኩልነቱን ተገፈፈ ማለት ነው። እነዚህ ባህርያት **በሕግ የተከለከሉ ናቸው፤ ከባድ የዲስፕሊን ጥሰትም** ናቸው።
- ጾታዊ ትንኮሳን እና ጥቃትን ለመከላከል የወጣው የ Technion የሥነ ምግባር ደንብ፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃትን ለመከላከል እና የተከበረ ድርጅታዊ ባህልን ለማዳበር በ Technion የተወሰዱ እርምጃዎችን ያስቀምጣል። እነዚህ እርምጃዎችም ግንዛቤ መፍጠር እና የቅሬታ ማቅረቢያ ስርዓት መዘርጋትን ያካትታሉ። የስነምግባር ደንቡ ዓላማ ህግን እና ደንቦቹን ለማገዝ እንጂ ለመተካት አይደለም።
- **ይሄ ደንብ ማን ላይ ነው ተፈጻሚነቱ?** የስነምግባር ደንቡ ተፈጻሚነት አንድ የ Technion ሰራተኛ በሌላው ላይ የሚፈፀመው ጾታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት፣ እና ድርጊቱ የተፈጸመው በ Technion ንብረት ላይ ወይም የ Technion ስራዎች ሲሰሩ ከሆነ፣ አንድ የ Technion ሰራተኛ የድርጅቱ ሰራተኛ ባለሆነ ሰው ላይ በሚፈጽመው ማንኛውም ትንኮሳ ወይም ጥቃት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ("የ Technion ሰራተኛ" ፍቺን ከዚህ በታች ይመልከቱ)።
- ***<u>ጾታዊ ትንኮሳ ምንድን ነው</u>***? የሚከተሉት ድርጊቶች የጾታዊ ትንኮሳ መገለጫዎች ናቸው፡-
  - o ጾታዊ ምላሽ ለማግኘት ማስገደድ፤
  - o ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶች — የወሲብ ስሜትን፣ እርካታን ወይም ስድብ ላይ ያነጣጠሩ ድርጊቶች፤
  - o ባህሪው የማይፈለግ መሆኑን ግልጽ ያደረገ ሰው ላይ ተደጋጋሚ የጾታዊ ግንኙነት ሃሳብ ማቅረብ፤ ትንኮሳው የተፈጸመው ስልጣን ወይም ሃላፊነት ባለው ሰው ከሆነ፣ አለመፈለግን ወይም ተቃውሞን የማሳየት ግዴታ የለም፣ በሥነ ምግባር ደንቡ መሠረትም፣ ጥያቄው የግድ መደጋገም የለበትም።
  - o ትኩረቱ የማየፈለግ መሆኑ እየተነገረው ስለ አንድ ሰው የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ተደጋጋሚ ማጣቀሻዎችን መሰንዘር። እነዚህ ተደጋጋሚ ማጣቀሻዎች የሚሰነዘሩት ስልጣን ወይም ሃላፊነት ካለው ሰው ከሆነ፣ ግለሰቡ አለመፈለጉን እና/ወይም ተቃውሞውን ባይገልጽም እንኳን፣ ይህ ተደጋጋሚና ያልተፈለገ ትኩረት ጾታዊ ትንኮሳ ነው።
  - o አንድን ሰው በጾታው፣ በጾታዊ ወይም ጾታዊ ዝንባሌው ምክንያት ክብረ ነክ ወይም አዋራጅ በሆነ መንገድ ማየት፤
  - o የአንድን ግልሰብ ጾታዊነት የተመለከተ ፎቶ፣ የቪድዮ ክሊፕ ወይም ቅጂ፣ የግለሰቡን ክብር ለመንካት የታለመ ከሆነና ሕትመቱም በቅን ልቡና ያልተዘጋጀና የግለሰቡ ፈቃድ ያልተሰጠው ከሆነ።
- ***<u>ትንኮሳ ያልሆነ ምንድን ነው</u>***? በጋራ መከባበር፣ በነጻ ፈቃድና በጋራ ስምምነት መንፈስ በቅን-ልቡና የተመሰረቱ አክብሮት አዘል ግንኙነቶች እንደ ጾታዊ ትንኮሳ አይቆጠሩም።
- ***<u>ጥቃት ምንድን ነው</u>***? ጥቃት ማለት አንድ ተማሪ፣ የፋኩልቲ አባል፣ ሰራተኛ ወይም አመልካች ከሚከተሉት ሁኔታዎች በሚመነጭ ምክንያት በሰራተኛ ወይም የስራ ሃላፊ ጉዳት ሲደርስበት ነው፡-
  - o ጾታዊ ትንኮሳ
  - o ጥቃት ወይም ጾታዊ ትንኮሳን የተመለከተ ሪፖርት፣ ቅሬታ፣ ምስክርነት ወይም ሕጋዊ እርምጃ
  - o ጾታዊ ትንኮሳን ወይም ጥቃትን የተመለከተ ቅሬታ ወይም ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ አንድ ሰራተኛ ሌላን ሰራተኛ ሲያግዝ።

- ***<u>ጾታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት የሚስተናገድበት መንገድ፡-</u>*** አንድ ግለሰብ ጾታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት ተፈጽሞብኛል የሚል ስሜት ከተሰማው፣ ከሚከተሉት ሶስት መንገዶች **በሁሉም ወይም በተወሰኑት** አማካይነት እርምጃ መውሰድ ይችላሉ፡-
  - o **የዲስፕሊን ሒደቶች፡-** ቅሬታ አቅራቢዎች አንዱን የ Technion የጾታዊ ትንኮሳ መከላከያ ኮሚሽነር ወይም ከቅሬታው ጋር አግባብነት ያለውን የ Technion ዘርፍ አስተባባሪ ማናገር ይችላሉ። መገናኘቱ በአካል፣ በቃል ወይም በጽሁፍ ሊሆን ይችላል።
  - o **የወንጀል ክስ ሒደት፡-** ለፖሊስ አቤቱታ ማቅረብ።
  - o **የፍትሐ ብሔር ሒደት፡-** የፍትሐ ብሔር ክስ መመስረት።
- ***<u>የጾታዊ ትንኮሳ መከላከያ ኮሚሽን፡-</u>*** Technion ጾታዊ ትንኮሳን ለመከላከል ኃላፊነት ያለባቸው ሶስት ኮሚሽነሮች አሉት፤ የTechnion ሰራተኞች ከጾታዊ ትንኮሳ/ጥቃት/ማዋረድ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችንና ጉዳዮችን ለእነርሱ ማቅረብ ይችላሉ። ኮሚሽነሮቹ በሥነ ምግባር ደንቡ ላይ በተገለጸው አሰራር መሰረት ጉዳዩን መርምረው ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው የሚለውን ለሚመለከታቸው የቴክኒካል ባለስልጣናት ይመክራሉ። በተጨማሪም፣ አስተባባሪ ኮሚሽነሮች ጾታዊ ትንኮሳን ለመከላከል ስልጠና እና ምክር ይሰጣሉ። በ Technion የሕክምና ፋኩልቲ ውስጥ ለጾታዊ ትንኮሳ የተለየ ኮሚሽነር አለ።
- ***<u>ጾታዊ ትንኮሳን የመከላከል አስተባባሪዎች</u>*****፡-** ከኮሚሽኑ ጋር አብረው የሚሰሩ ብዙ የፆታዊ ትንኮሳ መከላከል አስተባባሪዎች አሉ። አስተባባሪዎቹ **ለቅሬታዎች አፋጣኝ እና ተደራሽ አድራሻ** ሆነው ያገለግላሉ እንዲሁም **ከመከላከል ጋር በተያያዙ ስልጠና እና ተግባራት ላይ ያግዛሉ**። አስተባባሪዎቹ ቅሬታዎችንና ጥያቄዎችን የማስተናገድ ብቃት ስለሌላቸው፣ **ቅሬታዎችን** ቅሬታ አቅራቢው ወደሚፈልገው **ኮሚሽነር ማስተላለፍ አለባቸው።**
- ***<u>ቅሬታዎችና ችግሮች የሚስተናገዱባቸው አሰራሮች፤ ኮሚሽነሮች የማጣራት ስራ ሲያካሂዱ የማገዝ ግዴታ፡-</u>*** ኮሚሽነሮች የማጣራት ስራቸው ሚስጥራዊና ጥልቅ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፣ እናም የሚመለከታቸውን አካላት መብት ይጠብቃሉ። ስለ ጾታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት መፈጸም ጉዳይ ለ Technion ሰራተኛ ሪፖርት ከተደረገ፣ **ሰራተኛው ጉዳዩን ራሳቸው ማስተናገድ አይችሉም እና ወዲያውኑ** ለኮሚሽነር ***ሪፖርት ማድረግ አለባቸው***። ሁሉም የ Technion ሰራተኞች ከኮሚሽኑ ጋር ሙሉ ትብብር ማድረግና ለስራው አስፈላጊውን እገዛ መስጠት አለባቸው። ለምሳሌ፣ መረጃ ባለመስጠት ወይም ሐሰተኛ መረጃ በመስጠት ከኮሚሽኑ ጋር አለመተባበር በሕግ ካልታገደ በስተቀር የዲስፕሊን ጥሰት ነው።
- ***<u>የማጣራት ስራ መጠናቀቅ / ቅሬታ፡-</u>*** የምርመራ ስራ ሲጠናቀቅ፣ ጉዳዩን የያዘው ኮሚሽነር "ስልጣን ላለው አካል" ቀጣዩን ምክረ ሃሳብ ይሰጣል፡- ጉዳዩ እንዲዘጋ፣ ትእዛዝ እንዲሰጥ፣ ማስጠንቀቂያ፣ ተግሳጽ፣ ጊዜያዊ እገዳ፣ ጥቃት ፈጻሚው ላይ የዲስፕሊን እርምጃ እንዲወሰድ ሃሳብ መስጠት፣ ሁለቱ ወገኖች እንዲለያዩ ሃሳብ መስጠት፣ እንደዚሁም ኮሚሽነሩ ተገቢ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ሁኔታውን መሰረት ያደረጉ ሌሎች እርምጃዎች እንዲወሰዱ ምክረ ሃሳብ ሊሰጥ ይችላል። የመጨረሻ ውሳኔ የሚወሰነው በ Technion ስልጣን ያለው አካል ሲሆን፣ ይህም ጥቃት አድራሹ እነደሚገኝበት የስራ ዘርፍ ይለያያል፡- ለተማሪዎች፣ የዩኒቨርሲቲው ሲኒየር ምክትል ፕሬዚዳንት፤ ለፋኩልቲ አባላት፣ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት፤ ለአስተዳደር ሰራተኞች፣ የሰው ሐብት ዳይሬክተር፤ ለሌሎች፣ የኦፕሬሽን ምክትል ዳይሬክተር ናቸው።